## <u>የ2001 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት</u>

1. ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ፡ ከሐምሌ 2000 እስከ ሰኔ 20/2001
2. የታቀዱና የተከናወኑ ቁልፍ፣ አበይትና ንኡስ ውጤቶች

### 2.1 የታቀዱ ግቦችና ቁልፍ ውጤቶች

- በተጠኑ ሰባት ሴክተሮች ሙሉ በሙሉ የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በመተግበር የመጣ ተቋማዊ ለውጥ
- በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የኢንስፔክሽን አደረጃጀትና የአሠራር ስርዓት
- ህ/ሰብን በግልና በጋራ ስራ የማሣተፍ አሣምና ማሠራትን ባህል ለማዳበር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራርና ሞዴል የመጠቀም የተዘረጋ ስርዓት
- የህ/ሰብን ሠላምና ጸጥታ ለመጠበቅ ፈጣንና ፍታዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ስርዓት
- የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን ለሚተገብሩ ተቋማት፣ የስራ ሂደቶች እንዲሁም እስከ ቀበሌ ድረስ የተዘረጋ የመረጃ አውታሮች ስራዎች፤ የጥገናና የሰው ኃይል ስልጠና፤
- የተገልጋይን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል የተዘረጋ እቅድ ዝግጅት የአፈጻጸም የክትትልና ግምገማና የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት፤

### 2.2 የተከናወኑ ቁልፍ ውጤቶች

#### 2.2.1 በተጠኑ ሰባት ሴክተሮች ሙሉ በሙሉ የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በመተግበር የመጣ ተቋማዊ ለውጥ፣

- በዞኑ ውስጥ የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የሚፈጽሙ ሴክተሮች ወደ ተግባር ከመግባታቸው በፊት በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የዞንና የወረዳ ባለሙያዎች የ02 ቀን ውይይት በማድረግና በጉደዩች የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ እስከ ታችኛው እርከን ድረስ የመንግስት ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።
- ከክልል በተላከው የመሠ/ሂደ/ለውጥ ትግበራ ስትራቴጂን የሠራተኛ ድልድል ደንብ ላይ ለዞንና ለወረዳ አመራሮች የ01 ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ኦረንቴሽን በመስጠት እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ የድልድል ኮሚቴዎች በድልድል አፈጻጸም ላይ ኦረንቴሽን ተሰጥቶ ድልድልና ምደባ ለማከናወን ተችሏል።
- በአጠቃላይ በዞንና በወረዳ በተፈቀዱ የስራ ሂደቶች ላይ 754 ሠራተኞች እንዲመደቡ የተደረገ ሲሆን፤

- የሰው ኃይል ከማሟላት አንጻር ከከፍተኛ ተቋማት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ 133 አልካቾች እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡
- በድልድል ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሠረት በየሴክተሮቹ በተለያዩ ምክንያቶች ምደባ ያልተሰጣቸው ብዛት 221 ሠራተኞች የነበሩ ሲሆን ከየሴክተሩ ኃላፊዎች የተውጣጣው የአማራጭ አፈላላጊ ግብረ ኃይል መሠረት 33 ሠራተኞች ከትምህርት ዝግጅታቸውና የስራ ልምድ አንጻር በሚመጥኑበት የስራ ሂደት ውስጥ በየሴክተሮች ምደባ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ምደባ ካላገኙት ሠራተኞች ውስጥ በርቀት ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉና በ2001 ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁ 7 ሠራተኞች ምደባ እንዲሰጣቸው ምደባ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- በአጠቃላይ ምደባ ካልተሰጣቸው ሠራተኞች ውስጥ 14 ሠራተኞች በድልድል ደንቡ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ውጤታቸው ከ50% በታች የሆኑ ሲሆን ቀሪዎቹ 167 ሠራተኞች ደግሞ የትም/ዝግጅታቸው ዝቅተኛነትና በሌሎች ምክንያቶች ምደባ ያልተሰጣቸው ናቸው፡፡
- በዞንና በወረዳ በዋና የስራ ሂደት ላይ የተመደቡ ሠራተኞች በክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ አማካይነት የተዘጋጀውን ስልጠና በሐዋሣና በሆሣእና ከተማ የተከታተሉ ሲሆን፤ በደጋፊ የስራ ሂደት ላይ የተመደቡ ሠራተኞች በዞን ደረጃ በአቅም ግንባታ መምሪያ ባለቤትነት 59 የሰው ኃብት ስራ አመራር፣ በፋ/ኢ/ል/መምሪያ 89 በልማት እቅድና መጃ ባለሙያዎች፤ በግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ባለቤትነት 71 በኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና 72 የህብረት ስራ ባለሙያዎች እንዲሁም በፍትህ መምሪያ 26 በወንጀል መከላከል ከክልል ሰልጥነው በመጡ የዞን ባለሙያዎች ስልጠናውን ለመስጠት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የአመራሩን አቅም ለማጎልበት በመልካም አስተዳደር መርሆችና በአመራርና በመፈጸም  ክህሎት ለ276 የአመራር አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከመሠረታዊ የስራ ሂደት ትግበራ ጋር በተያያዘ የቢሮ አደረጃጀት ከማስተካከልና አመቺ ከማድረግ አንጻር ከአቅም ግንባታ ህንጻ የባህልና ማስታወቂያ መምሪያ፣ ከገጠር ልማት ህንጻ የሴቶች ጉዳይ መምሪያ እንዲሁም ከፋ/ኢ/ል/መምሪያ ህንጻ ወጣቶችና ስፖርት እንዲወጡና ቀድሞ የወራቤ ከተማ አስተዳደር ከነበረበት ህንጻ በኪራይ እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡
- በዚህም መሠረት በየሴክተሮች ካሏቸው የስራ ሂደትና የባለሙያዎች ብዛት አንጻር ሰፋፊ ክፍሎች የሚያስፈልጋቸውንና ስራን ለማቀላጠፍ በአንድ ክፍል መኖር የሚባቸው ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ ይረዳ ዘንድ የቢሮዎች ግድግዳ

ማፍረስና የማገናኘት ስራዎች እንዲሁም ሠፋፊ ክፍሎችን በመስታወት በመከፋፈል ለአገልግሎት አሰጣጥ አመቺ እንዲሆን ተደርጓል።

- ከሰው ኃብት ልማት አንጻር ከዞናችን በአርባን ማኔጅመንት የድህረ ምረቃ ፕሮግራም 02 እጩዎች ተመልምለው ወደ ሲቪል ሠርቪስ ኮሌጅ የመግቢያ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል። ለመጀመሪያ ዲግሪ መርሃ ግብርም የርቀት ትምህርት መርሃ ግብር በፐብሊክ ማኔጅመንት 07 ሠዎች በመደበኛው መርሃ ግብር ለ2ኛ ዲግሪ በተሰጠው የትም/እድል የመግቢያ ፈተናውን ከተፈተኑት ውስጥ 02 ሠራተኞች ያለፉ ሲሆን በመጀመሪያ ዲግሪ እንደዚሁ 02 ሠራተኞች አልፈው ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ። 14 እጩ በአርባን ኢንጂነሪንግ ተመልምለው ለመግቢያ ፈተና ዝርዝራቸው እንዲለይ ተደርጓል። 6 እጩዎች በደቨሎኘመንት ኢኮኖሚክስ፣ በፐብሊክ ፋይናንስና በህግ ለድህረ ትምህርት በተሰጠው እድል መሠረት ምዝገባ እየተከናወነ ይገኛል።

**2.2.2 በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የኢንስፔክሽን አደረጃጀትና የአሠራር ስርዓት**

**2.2.3 ህ/ሰብን በግልና በጋራ ስራ የማሣተፍ አሣምኖ ማሠራትን ባህል ለማዳበር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የአሠራርና ሞዴል የመጠቀም የተዘረጋ ስርዓት**

- ህ/ሰቡን በግልና በጋራ የማሣተፍና አሣምኖ ማሠራትን እንዲሁም ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለመዘርጋት በታቀደው መሠረት በፓኬጁ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በ8ቱም ወረዳዎች የሞዴል አርሶ አደሮች የማብቃት ስራ ተካሂዶ ሞዴሎች ተከናውኗል። እንደዚሁም በ2000 አፈጻጸም ረገድም ለሞዴል አርሶ አደሮች የማትጊያ ሽልማት ለሁሉም ወረዳዎች ተሰጥቷል፡
- መልካም ተሞክሮችንን ለማስፋት ይቻል ዘንድ ክልሉ በላከው ቢጋር ላይ 01 ቀን ውይይት ተካሂዶ የቅመራ ስራ የሚያከናውን ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ተግባር ተገብቷል። በ8ቱም ወረዳዎች የሚገኙትን 178 የገጠር ቀበሌዎች ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች አንጻር የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ተካሂዶ በደረጃ የመለየት ስራ ተከናውኖ በመልካም ተሞክሮዎች በየቀበሌው እንዲስፋፋ የቅመራ ሠነዶች ተሰራጭተዋል።
- በዞንና በ8ቱ የወረዳ ሴ/መ/ቤቶች የሲቪል ሠርቪስ ሪፎርም ትግበራ አንጻር የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ከክልል አቅም ግ/ቢሮ በተላከልን ቼክ ሊስት መሠረት ተሰርቶ በደረጃ መለየት ተችሏል። በተጨማሪም በዞን፣ በወራቤ ከተማ

አስተዳደርና በ8ቱ ወረዳዎች የሚገኙ የፍትህ ተቋማት የፍትህ ማሻሻያ ኘሮግራም አፈጻጸም ረገድ የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ተካሂዷል፡፡

- በ178 የገጠር ቀበሌዎች የቀበሌ እቅድ ተዘጋጅቶ በህ/ሰቡ ውይይት ተደርጐበትና ጸድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ እንደዚሁም እያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ አርሳ አደር የ2001 እቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጐ ድጋፍና ክትትል እየደረገ እቅዱን በተግበር ላይ ይገኛል፡፡
- በ176 የገጠር ቀበሌ ስራ አስኪያጆች በቀበሌው ጽ/ቤት የሚያከናውኗቸው ስራዎች አንጻር የውጤት ተኮር እቅድ አዘጋጅተው ከበላይ አካላት ጋር ተፈራርመዋል፡፡
- በገጠር ቀበሌዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ የተቀጠሩት ስራ አስኪያጆችና እንዲሁም የቀበሌ ሊ/መ/ር በስራ አሠራርና የስራ ኃላፊነት ግንዛቤ ከማስጨበጥ አኳያ የመረጃ ልውውጥ የተደረገ ሲሆን ከዚህም አንጻር አቅማቸውን ከማጐለበት አኳያ በእቅድ ዝግጅትና በአገ/ት አሰጣጥ ግንዛቤ በሁሉም ወረዳ እንዲሰጥ ታቅዶ በሣራኩራ፣ በምእራብ አዘርነት በርበሬና በዳሎቻ ወረዳ ለገጠር ቀበሌ ሊቀመንበር ጨምሮ የ02 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል እንዲሁም በምስራቅ አዘርነትና በስልጢ ወረዳዎ
- ች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ እንዲሁም ከዳሎቻ ወረዳ በስተቀር ለ156 የገጠር ቀበሌ ስራ አስኪያጆች በአመራር ክህሎትና በማስፈጸም አቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በሣንኩራ ወረዳ ለ29 የገጠር ቀበሌ ስራ አስኪያጆች በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ትግበራ ለ03 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**2.2.4 የህ/ሰብን ሠላምና ጸጥታ ለመጠበቅ ፈጣንና ፍታዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ስርዓት**

- በዞን ደረጃ የፍትህ አካላት /ዳኞች፣ አቃቢያንና ፖሊሳች/ ያካተተ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ አተገባበር ላይ በዋና አስተዳዳሪነት ሰብሳቢነት የ01 ቀን ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህም በየወረዳው የነበሩ የአሠራር ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- በሁሉም የከተማና የገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲኒንግ እንዲጠናከር ከማድረግ አኳያ በየጊዜው ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

2.2.5 **የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን ለሚተገብሩ ተቋማት፣ የስራ ሂደቶች እንዲሁም እስከ ቀበሌ ድረስ የተዘረጋ የመረጃ አውታሮች ስራዎች፣ የጥገናና የሰው ኃይል ስልጠና፤**

- በወረዳ ኔት ማእከላት ውስጥ የሚገኙ ብልሽት ለገጠማቸው መሣሪያዎች በስልጢ ወረዳ ጥገና የተካሄደ ሲሆን በሣንኩራ ወረዳ ቀደም ሲል መሣሪያዎቹ ተቀምተው ከነበሩበት ምቹ ያልሆነ ክፍል ወጥተው አዲስ በተገነባው ክፍል በማዛወር ተከላ ተካሂዷል፡፡
- የኢኮቴን መሠረተ ልማት አገልግሎት ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ ለ6 ወረዳዎችና ለ1 ከተማ አስተዳደር በሙያው የሰለጠኑ 8 ባለሙያዎች ቅጥር ተፈጽሞ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡
- በምእ/አዘ/በርበሬ ወረዳ ለ28 የወረዳ አመራሮች መሠረታዊ የኮምፒዩተር አጠቃቀም ስለጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በሣንኩራ ወረዳ 9 የገመድ አልባ ስልኮች ብልሽት ተከስቶ በባለሙያዎች ጥገና ተካሂዶ ሁሉም አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡
- በዞን ሴ/መ/ቤቶች ውስጥ የሚገኙት ኮምፒዩተሮችና ኘሪንተሮች መረጃ በማሰባሰብ አገልግሎት የማይሰጡት ጥገና እንዲደረግላቸው ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

2.2.6 **የተገልጋይን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል የተዘረጋ እቅድ ዝግጅት የአፈጻጸም የክትትልና ግምገማና የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት**

- በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ትግበራ ላይ እስከ ቀበሌ ድረስ በመውረድ የድጋፍና ክትትልና ግምገማ ተደርጓል፡፡
- የመሠረታዊ የስራ ሂደት ትግበራ ስርዓት ባለው መልኩ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ለውጡን ተቋማዊ መሰረት ለማስያዝ በዞን ደረጃ ከየሴክተሩ የተውጣጣ የድጋፍ ኃይል በማደራጀት በዞኑ ሴክተር መ/ቤቶች አፈጻጸም ውይይት የተደረገ ሲሆን ሁለት ዙር በወረዳ በመንቀሳቀስ በአፈጻጸም ያጋጠማቸው ችግር ላይ ውይይት በማድረግ የመፍትሔ ሃሣቦች እንዲሁም በየወረዳው በመገኘት ከወረዳው አመራር አካላት ጋር በግብረ መለስ የዳበረ ውይይት ተደርጓል፡፡

***<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>***

- ከፍተኛ የሆነ የኮምፒዩተርና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች እጥረት
- ለሴክተሩ የሚመደብለት በጀት አነስተኛ መሆን
- ከክልል ይላካሉ ተብለው ቃል የተገቡ ያልተላኩ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች
- የክልሉ ተከታታይነት ያለው የድጋፋዊ ክትትልና ግሣገማ ማነስ
- የተጠናከረና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስራ ተጠናክሮ ያለመዘርጋት
- የእቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ምዘና ወጥነት ያለው ስርዓት ያለመዘርጋት

**የአቅም ግንባታ የ2001 የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት**

የአቅም ግንባታ ስራዎችን በተመለከተ በተጠኑ ሰባት ሴክተሮች መ/ቤቶች ሙሉ በሙሉ የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ለመተግበር የታቀደ ሲሆን በነዚህም 7 ሴክተሮች ወደ ሙሉ ትግበራ ከመገባቱ በፊት ለሁሉም የዞንና ወረዳ የመንግስት ሰራተኛ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ-ሀሳብ ላይና በአስፈላጊነቱ ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በተዘጋጀው የትግበራ ስትራቴጂውንና የሠራተኛ ድልድል ደንብ ለዞን ለወረዳ አመራሮች የግንዛቤ ስልጠና በመስጠት እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ የድልድል ኮሚቴዎች በድልድል አፈጻጸም ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ በማድርግ ምደባና ድልድሉ ግልጽ በሆነ አሰራር ተከናውኗል፡፡በዚህም የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ አደረጃጀት በትምህረት ዝግጅት ማነስና በመስፈርቱ መሰረት በምደባው ያልተካተቱ ሰራተኞችን የረጅም ጊዜ ስልጠና የሚያገኙ በማቋቋም እንዲሁም በጡረታ የሚሸኙትን የመለየት ስራ ተከናውኗል፡፡እንዲሁም በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተመደቡ ሰራተኞች በመውሰድ ወደ ሙሉ ትግበራው እንዲገቡ ተደርጎዋል፡፡

የቢሮ አደረጃጀት ከማስተካከልና አመቺ ከማድረግ አንጻር በየሴክተሮች ካሏቸው የስራ ሂደትና የባለሙያዎች ብዛት ፤ ሰፋፊ ክፍሎች የሚያስፈልጋቸውንና ስራን ለማቀላጠፍ በአንድ ክፍል መኖር የሚገባቸው ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ ይረዳ ዘንድ የቢሮዎች ግድግዳ ማፍረስና የማገናኘት ስራዎች እንዲሁም ክፍሎችን በመስታወት በመከፋፈል ለአገልግሎት አሰጣጥ አመቺ እንዲሆን ለማድረግ ሰፊ ጥረቶች ተደርጓል፡፡

በዋናነት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሊቀለበስ የማይችልና ተቋማዊ መሰረት እንዲይዝ ለማድረግ የድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ስርአት ባለው መልኩ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ዞን ሴክተሮችና ወረዳዎች ያለውን አፈጻጸም ከላይ ድጋፊዊ ግምገማ እና ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በታዩ ክፍተቶች ላይ ከወረደው ቸመራር አካላት ጋር ግብረ-መልስ በመስጠት በክፍተቶች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡

በዞኑ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳዳር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ የኢኒስፔክሽን አደረጃጃትና የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት በቀበሌ ደረጃ የቡድኑን አባላት በተመለከተ ግልጽነት ተፈጥሮ ቡድኑ እንዲዋቀር የተደረገ ሲሆን በፓኬጁ መሰረት በተፋጠነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ተገርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ በመውረድ የልማትንና የመልካም አስተዳደር እቅዶችን ለማሳካት ጥረት ተደርጓል፡፡

ህ/ሰቡን በግልና በጋራ የማኅተፍና አሣምኖ ማሠራትን ልምድን ለማደበርና ግልጽና ተጠያቂነት ያለውየአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የታቀደ ሲሆን ይህንንም ግብ ለማሳካት በ8ቱም ወረዳዎች የሞዴል አርሶ አደሮችን ለመፍጠር በተደረገው ጥረት አርሶ አደሩ ለላቀ ልማት ለማነሳሳት የልማት አርበኛ አርሶ አደሮችና ባለሙያዎች በመልካም አሰተዳደር ፓኬጅ መመሪያ መሰረት እንዲለይ በማድረግ የማበረታቻ ሽልማት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች አንጻር የተለዩ መልካም ተሞክሮዎች ላይ አንድ ሰነድ የተቀመረ ሲሆን ተሞክሮውንም ለማስፋት በየቀበሌው ሰነዱ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

በገጠር ቀበሌዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የቀበሌ ስራ አስኪያጆችና እንዲሁም የቀበሌ አመራር በስራ አሠራርና የስራ ኃለፊነት ግንዛቤ ከማስጨበጥና በእቅድ ዝግጅትና በአገ/ት አሰጣጥ እንዲሁም በማስፈጸም አቅም ግንባታ፤በአመራር ክህሎት በሁሉም ወረዳ በተለያዩ ጊዜያት ከአንድ እና አምስት ቀን የሚደርስ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የቀበሌ  ስራ አስኪያጆች በቀበሌው ጽ/ቤት ከሚያከናውኗቸው ስራዎች አንጻር የውጤት ተኮር እቅድ አዘጋጅተው እንዲፈራረሙ ተደርጓል፡፡

የህብረተሰቡን ሰላም ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍታሃዊ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የታቀደ  ሲሆን በዚህም መሰረት በዞን ደረጃ የፍትህ አካላት /ዳኛች፣ አቃቢያንና ፖሊሲች/ ያካተተ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ አተገባበር ላይ በሁለት ዙር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህም በየወረዳው የነበሩ የአሠራር ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሁሉም የከተማና የገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር ከማድረግ አኳያ የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

የሴክተሮችን የሰው ኃይል ፍላጎት ለሟሟላት በታቀደው መሰረት 133 ከከፍተኛ ተቋም ተመረቂዎች እንዲቀጠሩ የተደረገ ሲሆን በረጅም ጊዜ ስልጠና  በኢትዮጵያ ሲቪል ሠርቪስ ኮሌጅ 4 ለድህረ ምረቃ ፣ 7 ለመጀመሪያ ዲግሪ መርሃ ግብርም የርቀት ትምህርት፣ 2 ለመጀመሪያ ድግሪ በመደበኛ ፕሮግራም የትምህርት እድል ያገኙ ሲሆን፣14 ለመጀመሪያ ድግሪና 6 ለድህረ ምረቃ ትምህርት የመግቢያ ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን ለሚተገብሩ ተቋማትን በስልጠናና በቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ለማደራጀትና ኮምፒተሮችን ለመጠገን እንዲሁም እስከ ቀበሌ ድረስ የመረጃ አውታር ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት ከአንድ ሚሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ የኮምፔተርና የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ግዢ እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡እንዲሁም በገጠር ቀበሌዎች የሸቦ አልባ ስልኮችን በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍና ክትትል የተደረገ ሲሆን በመንግስት ተቋማት የተበላሹ ኮምፒውተሮች ጥገና ተደርጓል፡፡

የመንግስት ሠራተኞችን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል በታቀደው መሠረት 142 የመንግስት ሰራተኞች የመሰረታዊ ኮምፒዩተር ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡